# የነገን ማን  ያውቃል?

ከነቅዓ ጥበብ (ሐምሌ 2003)

የደቡብ ሱዳኑ፣ የነፃነት በዓል፣
ዛሬስ ደስ ብሎናል፣ የነገን ማን  ያውቃል?

የነገን ማን  ያውቃል፣ ተስፋፊ ቢነሳ፣
ምክንያት ፈልጎ፣ በቋንቋ በጎሳ።
በቋንቋ በጎሳ፣ ባጥሳኝ ምክንያት፣
እንደነ ወገዴ፣ ክልሉን ለማስፋት፣
ጊዜ የሰጠው ቅል፣ ድንጋዩን ሲሰብር፣
እንደወያኔ ጉድ፣ ሲያፈራርስ ድንበር፣
ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ያካባቢ ክልል፣
ወያኔ የሠራው፣ ጣጠኛው ክፍፍል፣
በደቡብስ በኩል፣ እንዳያመጣ እክል፣
ጥሰትናው ምንድነው፣ ጉዳዩ ተጢኗል?
ይህንስ አደጋ፣ ሠራዊቱ ያውቃል?

የኢትዮጵያ አንድነት፣ ሉዓላዊነቷ፣
የድንበሯ ክልል፣ የአገርነቷ፣
እንደ ሰሜን ሁሉ፣ በምሥራቅ በምዕራብ፣
ክልሎች ባሉበት፣ በወዲያም በደቡብ፣
የመገነጣጠል ጥያቄ ቢነሳ፣
በመልክ፣ ባካባቢ፣ በቋንቋ፣ በጎሳ፣
ህገ-መንግሥቱ እንደሁ፣ ይደግፋቸዋል፣
ብሄራዊው ሸንጎም፣ ባንድ ድምፅ ይነደል፣
ሰዎች አስቡበት፣ ይህ ነገር ያሠጋል፣
ነገ'ኮ ላይኖር ነው፣ ኢትዮጵያ የሚባል!

የህዋን ጨዋታ፣ የወያኔ ድካም፣
ሲቃትት ይታያል፣ በትኖ ለመለቀም።

ኢትዮጵያዊነትን የሚሸሸው ሁሉ፣
ሀበሻ ነኝ ይላል፣ ቢጠፋበት ሙሉ፤
ያበሻ ምግብ ቤት፣
ያበሻ ፀጉር ቤት፣
ያበሻ ልብስ ቤት፣
ያበሻ ጋራዥ ቤት፣
በሀበሻ ሽፋን፣ አደዲስ ስም ማውጣት፣

ፍፁም ለመሸሽ ነው፣ ኢትዮጵያን ለመካዴት።
ሀበሻ የሚሉት፣ ይህ አጼሶ ታርጋ፣
እያወላወለ፣ ሰው ሁሉ እንዲያረጋ፣
እንደ ክፉ አረቄ፣ አስክሮ ሊያላጋ፣
ጥሪኝ ቆሎ ይዞ፣ ወደ አሻሮ ጠጋ፣
ከኢትዮጵያ በላይ፣ የት ይገኛል ፀጋ!?
እነሱም አይጠሩ፣ በመንገድ ሲያገኙኝ፣
ያቅለሸልሸኛል፣ “ሀበሻ ነህ?” ሲሉኝ፣
ለተንኮል መሆኑ፣ ሴራው እየገባኝ።

ኩራቴን፣ ጋምቤላ፣ የተፈጠረው ጠንቅ፣
በወያኔ ሥርዓት፣ አይችልም ለመድረቅ።
ያው ያባቶች አምላክ፣ ካልጠበቃት በቀር፣
እኔንስ ጨንቆኛል፣ የኢትዮጵያ ነገር፣
ምንደኛው ወያኔ፣ ምናለ ዕድሜው ቢያጥር?!